# ምክር ቤቱ ለግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ምርመራ የሰጠው ምላሽ የምዕራፍ 2 ሪፖርት

ዲሴምበር 2024

THE ROYAL BOROUGH OF
KENSINGTON
AND CHELSEA

# ፲. የዋና ነጥቦች ማጠቃለያ

## መግቢያ

1 የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ምርመራ ምዕራፍ 2 ሪፖርት ረቡዕ ሰኔ 14 ቀን 2017 ከደረሰው የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) እሳት አደጋ በፊት፣ በአደጋው ወቅት እና ከአደጋው በኋላ የነበሩ የምክር ቤቱን (የካዉንስሉን) ስህተቶች ይገልጻል። ሰባ ሁለት ሰዎች ሊወገድ ይችል በነበረ አሳዛኝ ክስተት ሕይወታቸውን አጥተዋል ። ምክር ቤቱ ነዋሪዎችን ከአደጋ የመጠበቅ፣ የሚያሳስቧቸውን ነገሮች የማዳመጥና እርምጃ የመውሰድ እንዲሁም አደጋ ሲከሰት ውጤታማ በሆነ መንገድ ምላሽ የመስጠት መሠረታዊ ኃላፊነቶቹን ሳይፈጽም ቀርቷል ። ለእነዚያ ስህተቶች፣ እና ለደረሰ ጉዳት፣ ያለ ምንም ገደብ ይቅርታ እንጠይቃለን።

2 የምርመራዉን ዉጤቶች እንቀበላለን። ሪፖርቱ በተለያዩ መስኮች ያሉ ድክመቶችን ለይቷል:- አብዛኛውን ጊዜ በንቀት እና በግዴለሽነት የሚገለፅ ከነዋሪዎች ጋር ያለ ግንኙነት መበላሸት፤ እንደ ሕንፃ ቁጥጥር እና ድንገተኛ አደጋ ጊዜ ዕቅድ የመሳሰሉ ወሳኝ ተግባራት ላይ ሙያዊ ብቃት አለመኖር፤ እንዲሁም የአመራር እና የአስተዳደር ውድቀት።

3 ምክር ቤቱ እነዚህን ጉድለቶች ለመቅረፍ ከ 2017 ወዲህ ጉልህ ለውጦችን አድርጓል፤ እነዚህም በዚህ ሪፖርት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተዘርዝረዋል። በተለይም፤ የሚከተሉትን ጉዳዮች አከናውነናል:-

a. የምርመራ ክፍል 1 ሪፖርት ምክረ ሀሳቦችን ተግባራዊ አድርገናል።

b. ከነዋሪዎቹ ጋር ይበልጥ ቀጥተኛ ግንኙነት ለመመሥረት የመኖሪያ ቤት አገልግሎቶችን ወደ ውስጣዊ አስተዳደር መመለስን ጨምሮ፣ በመኖሪያ ቤቶች አስተዳደር ረገድ ጉልህ የሆኑ ለውጦችን አድርገናል።

c. የመኖሪያ ቤቶችን ለማሻሻል ደኅንነትን የ 374 ሚሊዮን ፓውንድ የካፒታል ሥራ ፕሮግራማችን ዋነኛ አካል አድርገናል።

d. በውጭ ባለሙያዎች የእሳት አደጋ ስጋት ግምገማ እንዲከናወን በማድረግ፣ የቤት ውስጥ የእሳት አደጋ መከላከያ ቡድን አቋቁመናል፣።

e. ለድንገተኛ አደጋዎች በተሻለ ሁኔታ ዝግጁ መሆናችንን ለማረጋገጥ፣ ከማኅበረሰቦች ጋር በመተባበር የአይበገሬነት ተግባራችንን አጠናከረናል።

f. ሠራተኞች ተገቢውን ስልጠና እንዲያገኙ እና ለደኅንነት ቅድሚያ እንዲሰጡ ለማስቻል በህንፃ ቁጥጥር ረገድ ጉልህ ለውጦችን አድርገናል።

g. በአከራዮች ምክክር ኮሚቴ እና በሌሎች ሸንጎዎች/ፎረሞች አማካይነት ነዋሪዎች በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ እንዲሳተፉ አድርገናል።

h. ነዋሪዎች በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ እንዴት እንደሚሳተፉ የሚያሳይ የሕዝብ ተሳትፎ ቻርተር አዘጋጅተናል።

i. በምክር ቤቱ አጠቃላይ የስራ አፈጻጸም እና ምክር ቤቱ ቃል የገባቸውን ጉዳዮችን በማከናወን ረገድ ያሉ መሻሻሎችን በተመለከተ ለተመረጡ አባላት እና ለሕዝብ በመደበኛነት ሪፖርት ማድረጉን አረጋግጠናል።

4 የምዕራፍ 2 ሪፖርት ከወጣበት ጊዜ አንሥቶ በአደጋው ሰው ከሞተባቸው፣ ከአደጋው በሕይወት ከተረፉ እና ከማኅበረሰቡ ጋር ያደረግነው ውይይት በቂ ነዋሪዎች ከ 2017 ወዲህ ያደረግናቸውን ለውጦች እንዳልታያቸዉ እና እንዳልተሰማቸው ያሳያል። ስለ ደህንነት፣ ስለምንሰጠው የአገልግሎት ጥራት፣ ስለ ማኅበራዊ እና የዘር ማግለል/መድልዎ፣ ስለ የመስማት እና የመማር ፍላጎታችን በተመለከተ በአደጋው ሰው ያጡ ቤተሰቦችን፣ ከአደጋው በሕይወት የተረፉ ሰዎችን እና የነዋሪዎችን ስጋት ሰምተናል። አንዳንዶች ሁኔታዎች እየተባባሱ እንዳሉ የሚሰማቸው ሲሆን ሌሎች ደግሞ ምክር ቤቱ ለለውጥ ባለው አቅም ላይ እምነት አጥተዋል።

5 ለምርመራዉ ግኝቶች ምላሽ ለመስጠት፣ ተግባራቶቻችንን እና ቃል ኪዳኖቻችንን ከመዘርዘር የበለጠ ማድረግ ይኖርብናል። እንዴትና ለምን እንደወደቅን መረዳት አለብን ። አንዳንድ ጊዜ ምክር ቤቱ ነዋሪዎቻችንን በተለይም እኛ ላይ ተስፋ የሚያደርጉትን ለማገልገል ያለውን መሠረታዊ ዓላማ እንደ ሕዝብ አገልጋይ እንደዘነጋ ማስረጃው ያሳያል። ነዋሪዎችን በማዳመጥና በሕይወታቸው ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ውሳኔዎች ውስጥ በማሳተፍ ረገድ አልተሳካልንም፤ ተገቢ የቁጥጥር እና የተጠያቂነት ሥርዓቶች አልነበሩንም፤ እንዲሁም የሰዎችን ደኅንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሙያዊ ደረጃዎችን እና ቴክኒካዊ ብቃትን አልጠበቅንም። ምላሻችን ስለዚህ እነዚህን ውድቀቶች በቀጥታ የሚመለከቱ ሦስት ዋና ዋና መርሆዎች ላይ የተገነባ ነው:-

6 **የነዋሪው አቅም እና ተሳትፎ** – ዘላቂ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው ከህብረተሰባችን ጋር በሚፈጠር እውነተኛ አጋርነት ብቻ መሆኑን እንገነዘባለን። ይህም ማለት ነዋሪዎችን ከማማከር አልፈን ልምዳቸው እና ክህሎታቸው የምናከናውናቸው ስራዎችን እና የምናከናውንበትን መንገድ ቅርጽ እንዲሰጥ ለማድረግ የሚያስችሉ መንገዶችን መፈለግ ማለት ነው። በተጨማሪም በማኅበረሰባቸው፣ በተለይም በሰሜን ኬንሲንግተን (North Kensington) ከተመረጡ አማካሪዎችጋር ለመሥራት የሚያስችሉ አዳዲስ፣ ይበልጥ አካታች የሆኑ መንገዶችን መገንባትን ያካትታል። ይህን ስናደርግ፣ በምክር ቤቱ እና በሚያገለግላቸው ህዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት መልሶ መገንባትን ዓላማ አድርገን ነው።

7 **ገለልተኛ ግምገማ እና የአፈፃፀም ክትትል** – ለእራሳችን ግስጋሴ እራሳች ፈራጅ መሆን አንችልም። ስህተቶቻችን የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ እና በዚህም ምክንያት የሚከሰት የአመኔታ መቀነስን ከግምት በማስገባት፣ ውጫዊ ግምገማና የተጠያቂነት አሰራርን በአቀራረባችን ውስጥ ማካተት አለብን። ይህም በሕግ የተደነገጉ ደንቦችን ማክበርን እና በቁጥጥር ስራዎች ላይ በንቃት መሳተፍን፣ ውስጣዊና ውጪያዊ ኦዲቶች የሕዝቡን አመኔታ ለመጨመር በሚያስችል መንገድ ጥቅም ላይ ማዋልን እንዲሁም አዳዲስ ገለልተኛ ግምገማ እና የአፈፃፀም ክትትል አቀራረቦች መጠቀምን ያካትታል። በእነዚህ አመለካከቶች ላይ ተመሥርተን ለግምገማ እና ለዉጥን ለማድረግ ፍቃደኛ መሆን አለብን።

8 **ከፍተኛ ደረጃ እና የቴክኒክ ልህቀት** – ነዋሪዎቻችንን ለማገልገል ባለን ቁርጠኝነት ከፍተኛ የተናጠል የሙያ ብቃት እና የጋራ አገልግሎት ደረጃዎች ላይ የተመሰረተ ድርጅት ለመሆን ቃል እንገባለን። ይህም ማለት በሰራተኞች ምልመላ፣ ሥልጠና እና ማጎልበቻ ረገድ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ማለት ሲሆን፤ ግልጽ ደረጃዎችን እና ጠንካራ የአፈጻጸም አስተዳደር መዘርጋት፤ እንዲሁም እውቀትንና ብቃትን የሚደግፉና ሽላሚ ሥርዓቶችን መፍጠር ማለት ነው። ደረጃዎች ዘላቂ በሆነ መልኩ የሚጠበቁበት፣ ፕሮጀክቶች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ወጥ በሆነ ጥረት ፍጥነት እና ቅልጥፍና ተግባራዊ የሚደረጉበት፣ እንዲሁም ደህንነት፣ ምላሽ መስጠት እና ጥራት ከምቾት እና ወጪ በላይ ቅድሚያ የሚሰጡበት ባህል መፍጠር አለብን።

9 አንዴ የተፈጠረ ጉዳትን ተመልሰን እንዳልተፈጠረ ማድረግ አንችልም፣ ነገር ግን ከላይ እንደተጠቀሰው ዓይነት ባህል በመፍጠር በአደጋው ህይወታቸዉን ያጡ ሰዎችን ለመዘከር ከግሬንፌል (Grenfell) መታሰቢያ መመሥረት እንችላለን።

# አሥር ዋና ዋና ጭብጦች

10 በእነዚህ መርሆች በመመርኮዝ፣ ይህ ምላሽ በ 10 መስኮች የሚከናወኑ ተግባራትን ያስቀምጣል። በምርመራው ላይ የተመለከቱትን ልዩ ልዩ ጉድለቶች፣ ምክር ቤቱ ከ 2017 ወዲህ ያደረጋቸውን ለውጦች፣ የቀሩትን ክፍተቶች እና ድክመቶች ግምገማችንን፣ እና እነዚህን ለመቅረፍ የምንፈጽማቸውን ነገሮች በዝርዝር እናቀርባለን። እነዚያ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፦

## 11 የምክር ቤቱ መኖሪያ ቤቶችን ደኅንነት ማረጋገጥ

a. ከግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) የእሳት አደጋ ጋር የተያያዙ ተቋራጮች እና ምርቶች ላይ ያለንን እገዳ በማጠናከር ምክር ቤቱ ጥቅም ላይ አለማዋሉን እናረጋግጣለን፣ እንዲሁም የህንፃው ቁመት ምንም ይሁን ምን ለሁሉም የምክር ቤቱ ህንፃዎች እና የእደሳ ፕሮጀክቶች በውጭ ግድግዳዎች ላይ ተቀጣጣይ ቁሳቁሶች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ሙሉ በሙሉ እገዳ እንጥላለን።

b. ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎች በተመለከተ በዲፓርትመንቶች መካከል መረጃ ለመለዋወጥ የሚያስችል አዲስ ፕሮቶኮል ተግባራዊ እናደርጋለን ይህም የተናጠል ስጋት ግምገማ እና የአደጋ ግዜ ማምለጫ እቅድ እንዲሰጣቸው፣ እና በአስቸኳይ ጊዜ በአግባቡ እገዛ እንዲያገኙ ያስችላል።

c. ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎች ስለ መኖሪያ ቤት ደህንነት ያላቸዉ ተሞክሮን በተመለከተ እናነጋግራቸዋለን፣ ይህም በዳሰሳ ጥናቶች፣ በትኩረት ቡድን ውይይቶች እና በሌሎች ዓይነታዊ የምርምር ዘዴዎች አማካኝነት ጭምር የሚከናወን ይሆናል።

d. አሁን ላይ ያሉ የእሳት አደጋ ደኅንነት ሰነዶች ለሁሉም ነዋሪዎች እንዲደርሱ እና በተለያዩ ቋንቋዎች እንዲገኙ እናደርጋለን።

## 12 የተሻለ የቤት ባለቤት መሆን

a. በኬንሲንግተን (Kensington) እና በቼልሲ (Chelsea) የመኖሪያ ቤት አገልግሎቶችን በማግኘት እና በማቅረብ ረገድ ያሉ ተጨባጭ እውነታዎችን ለመዳሰስ፣ መሰናክሎችን እና ቊልፍ ጉዳዮችን ለመረዳት እና መፍትሄዎችን ለመለየት፣ ግኝቶቹን በመጠቀም የአገልግሎቶችን ዲዛይን እና አቅርቦት ለመቅረጽ ከነዋሪዎች እና ከመኖሪያ ቤት አገልግሎት አቅራቢ ሠራተኞች ጋር በመተባበር እንሠራለን።

b. አከራዮች፣ ተከራዮች እና በጊዜያዊ ማረፊያ ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች ቅሬታ ለማቅረብ እንዲችሉ የሚሰጣቸውን ድጋፍ እናሻሽላለን።

c. በማኅበራዊ ተከራዮች እና በጊዜያዊ ማረፊያ ውስጥ በሚገኙ ነዋሪዎች ላይ አዳዲስ ፖሊሲዎች የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ በእኩልነት ተጽዕኖው ተገምግሞ በምክር ቤቱ ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ በመደበኛነት ከግምት ውስጥ መግባቱን፣ የመኖሪያ ቤት ባለቤትነት ጥበቃ እንደሚደረግላቸው ሌሎች ባህሪያት በተመሳሳይ መንገድ መያዙን እናረጋግጣለን።

d. ተከራዮች፣ የሊዝ ባለይዞታዎች እና በጊዜያዊ ማረፊያ ውስጥ የሚገኙ ነዋሪዎች ምክር ቤቱ የሚሰጠውን አገልግሎት ወይም የሚሰጠው የአገልግሎት ጥቅም እንዲያውቁ እና በዚህ ረገድ የበለጠ እንከን የለሽ ልምድ እንዲኖራቸው በቤቶች እና ሌሎች መምሪያዎች መካከል ይበልጥ ውጤታማ የሆነ የሥራ ግንኙነት እንገነባለን።

## 13 መልሶ ግንባታ እምነት

**a.** ከነዋሪዎች ጋር ያለን ግንኙነት በሚናድበት ወቅት ገለልተኛ አቀላጣፊ እና አስታራቂ መጠቀምን ጨምሮ  መልሶ ማደሻ ዘዴዎች አዘውትረን እንጠቀማለን።

**b.** ከግሬንፌል (Grenfell) አሳዛኝ ክስተት ወዲህ ስለተወሰኑ ውሳኔዎች አብረን የምናሰላስልባቸውን መንገዶች እናገኛለን፣ የደረሰውን ጉዳት አምነን በመቀበል እና ከስህተቶች በመማር የወደፊቱ ውሳኔ አሰጣጥ ተጨማሪ ክፍፍልን አለመፍጠሩን እናረጋግጣለን።

**c.** መረጃዎችን እና የአፈፃፀም ውሂቦችን በግልጽ እናጋራለን፣ ነገሮች በተሳሳተ መንገድ ሲሄዱ ግልጽ እና ሐቀኞች እንሆናለን እንዲሁም ከባድ ውሳኔዎች ሲያጋጥሙን ገለልተኛ ግምገማ እና የአፈፃፀም ክትትል እና የነዋሪዎችን አስተዋጽኦን እንጋብዛለን።

**d.** ከፍተኛ አመራሮች ለሁሉም ክፍት በሚደረግ መድረክ፣ በመኖርያ ህንፃዎቹ የእግር ጉዞ በማድረግ እና መደበኛ ባልሆነ ስብሰባ፣ በተለይም በማኅበራዊ መኖሪያ ቤት ነዋሪዎች እና አመኔታ መልሶ መገንባት በሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች ላይ በማተኮር ከማኅበረሰቦች ጋር ቋሚ ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖራቸው እናደርጋለን።

## 14 የህንፃ ቁጥጥር እና የደህንነት ደረጃዎች

**a.** 100 በመቶ የህንፃ ቁጥጥር ሠራተኞች የሙያ እውቅና እና ሥልጠና እንዲኖራቸው እንዲሁም ስለሚኖሩ ለውጦች ለከፍተኛው አስተዳደር ሪፖርት ማድረጋቸውን እናረጋግጣለን።

**b.** መንግሥትን በብሔራዊ የህንፃ ቁጥጥር ዘርፍ ላይ የሚያደርገውን ግምገማ እንደግፋለን፣ እንዲሁም በተቻለ ፍጥነት ተግባራዊ የሚደረጉ ተሐድሶዎችንና ምክረ ሐሳቦችን ተቀብለን ተግባራዊ ለማድረግ እንዘጋጃለን።

## 15 የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት እና ምላሽ አሰጣጥ

**a.** የምርመራውን ምክረ ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እናደርጋለን፡-

- **i.** ሁሉም ሠራተኞች አይበገሬነት ዋነኛው ኃላፊነታቸው እንደሆነ አድርገው እንዲመለከቱ፣ እና እንቅስቃሴ ላይ አዘውትረው ለመሳተፍ ስልጠና ማግኘታቸውን በማረጋገጥ
- **ii.** በድንገተኛ አደጋ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ስርዓቶችን ለዓላማው ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በመከለስ
- **iii.** የተፈናቀሉ ነዋሪዎች በተቻለ ፍጥነት ፍላጎታቸውን የሚያሟሉ ማረፊያ ቦታዎች እንዲገኙ ለማድረግ የአስቸኳይ ጊዜ ማረፊያ እቅዳችንን በማሻሻል
- **iv.** የመገናኛ ጣቢያዎች እና የማረፊያ ማዕከላት ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ ለማቅረብ የሚያስችል ብቃት እንዲኖራቸው በማድረግ

**b.** በሁሉም የከፍተኛ መኮንኖች የስራ ኮንትራቶች እና መግለጫዎች ውስጥ የተወሰኑ የአይበገሬነት ኃላፊነቶችን እናካተታለን፣ ጥብቅ የሙያ ብቃት መስፈርቶች ማሟላታቸውን እናረጋግጣለን፣ እና በሁሉም የከፍተኛ ደረጃ የስራ ምልመላዎች ላይ የአይበገሬነት መስፈርቶችን እናካትታለን።

**c.** ምክር ቤቱ በዘርፍ 1 ምላሽ ሰጪነት የሚጫወተውን ሚና ለመደገፍ ብቁ ሆኖ እንዲቀጥል ለማድረግ የድንገተኛ አደጋ እቅድ አጠቃቀማችንን በተመለከተ የተሟላ ግምገማ እናደርጋለን።

**d.** ማህበረሰባዊ ትብብርን እናጠነክራለን፣ ከነዋሪዎች፣ ከአካባቢው የበጎ አድራጊ ድርጅቶች እና አማካሪዎች ጋር አብረን የምንሰራባቸውን መንገዶች እናጠናክራለን።

## 16 ማህበረሰባችንን መረዳት

**a.** አዲሱን ፍትሃዊ የተግባር እቅድ ተጠቅመን የነዋሪዎችን በተለይም የተለያየ ጎሳ ያላቸው ነዋሪዎችን እና የአካል ጉዳተኞችን ፍላጎትና የህይወት ልምድ ጠንካራ መረጃ ላይ በመመስረት እኩልነትን፣ ብዝሃነት እና አካታችነት የሚያስተናግድ አዲስ ፍትሃዊ ምክር ቤታዊ አቀፍ አቀራረብን እናዳብራለን።

**b.** በነዋሪዎች ፍላጎት እና ተሞክሮዎች ላይ የበለጠ ትኩረት በማድረግ በግምገማ እና ክትትል ላይ ይበልጥ ጠንካራ አቀራረብን በማካተት የእኩልነት ተፅዕኖ ግምገማዎች ላይ ያለንን አቀራረብ ሙሉ በሙሉ እንመርምራለን።

**c.** ስለ ማህበረሰባችን የተሻለ እና ዘላቂነት ያለው ግንዛቤን ለመገንባት እንዲቻል በምክር ቤቱ የሚቀጠሩ የአካባቢው ነዋሪዎች ቁጥር ከፍ ለማድረግ ተጨማሪ እርምጃዎችን እንወስዳለን።

**d.** በማኅበረሰቡ ውስጥ በተለይም በሰሜን ኬንሲንግተን (North Kensington) በቋሚ ክወናዎች፣ በሕዝብ የውይይት መድረኮች እና በሌሎች ፎርሞች ውስጥ ከፍተኛ አመራሮች ዕለት ተዕለት እንዲገኙ እናደርጋለን።

**e.** በሰሜን ኬንሲንግተን (North Kensington) እና በሌሎች ተመሳሳይ ተግዳሮቶች ባጋጠሟቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ነዋሪዎች ስላጋጠሟቸው ተሞክሮዎች የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለሁሉም አማካሪዎች የሚሰጠውን ሥልጠና ዳግም እንመረምራለን።

## 17 አጋርነትን እና ውሎችን ማስተዳደር

**a.** ለሁሉም ዋና ዋና ውሳኔዎች የደህንነት ግምገማ እንዲቀርብ በመጠየቅ፣ በኮንትራቶች ውስጥ የደህንነት መስፈርቶችን በማሻሻል፣ እና የደህንነት ጉዳዮችን ከፍ በማድረግ እንዲሁም እነዚህ ጉዳዮች የሚፋጠኑበት ግልጽ የሆነ አሰራር በመፍጠር ኮንትራቶችን በምናስተዳድርበት መስፈርት ውስጥ ደህንነትን እንደ ዋነኛ ጉዳይ አድርገን እናስቀምጣለን።

**b.** አዲስ የኮንትራት አስተዳደር ማዕቀፍ በመተግበር፣ የአፈጻጸም መረጃዎችን በስርዓት በመከታተል፣ እንዲሁም ኮንትራክተሮች አገልግሎቶችን እንዴት እየሰጡ እንዳሉ በየጊዜው ሪፖርት በማድረግ የኮንትራቶችን አፈጻጸም በምንከታተልበት አሰራር ላይ የበለጠ ጥብቅ እንሆናለን።

**c.** ኮርፖሬት የነዋሪ ግዥ ፓነል በመፍጠር፣ ነዋሪዎች ትርጉም ባለው መንገድ እንዲሳተፉ ለማገዝ ስልጠና በመስጠት፣ እንዲሁም ሙሉ የምክር ቤቱን የቅጥር ተግባራት የነዋሪዎች አመለካከትን እና ተሞክሮን መሰረት ያደረገ እንዲሆን በማድረግ ኮንትራክተሮችን እንዴት እንደምንመርጥ እና እንዴት እንደምናስተዳድር በተመለከተ ለነዋሪዎች አቀኛ ድምጽ እንሰጣለን።

**d.** ኮሚቴዎች ከደህንነት አንፃር ወሳኝ ለሆኑ እና ከፍተኛ የአደጋ ስጋት ላቸውኑ ኮንትራቶችን አዘውትረው እንዲመረምሩ በማድረግ፣ በተደጋጋሚ ምርመራ በማድረግ እና የኮንትራክተር አፈጻጸም መረጃዎችን በህዝብ ፊት እንዲያቀርቡ በማድረግ ውሎችን መቆጣጠርና መመርመር እናጠናክራለን።

## 18 የተካነ እና ፕሮፌሽናል የሰው ኃይል

**a.** በተለይ በቴክኒክ ብቃት፣ በደህንነት ግንዛቤ፣ በህዝብ አገልግሎት እና ሰብአዊነት ላይ በማተኮር ከግምገማዉ ግኝቶች አንፃር ሰራተኞችን እንዴት እንደምንመለምል፣ እንደምናሰማራ፣ እንደምናሠለጥን እና አፈጻጸምን እንዴት እንደምናስተዳድር የተሟላ ጥናት እናካሂዳለን። በሁሉም የሰው ኃይል ውስጥ ከፍተኛ ደረጃዎችን ተግባራዊ እናደርጋለን፤ እንዲሁም ባልተሟሉበት ቦታዎች ላይ እርምጃ እንወስዳለን።

**b.** ከፍተኛ የሙያ ብቃት ደረጃዎችን ለማስጠበቅ እንዲረዳን የግዴታ መስፈርቶች እና ሙያዊ ምዝገባዎች ግልጽ የሆነ ክትትል ባካተተ መልኩ የሁሉንም ሠራተኞች ብቃት እና ስልጠናዎች ለመከታተል አዳዲስ ስርዓቶችን ጥቅም ላይ እናውላለን።

c. በሰው ኃይል ምልመላ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ መስፈርቶች እድገት እንዲሁም በሰራተኞች አሰራር ላይ አስተያየት መስጠት እንዲችሉ በማድረግ ነዋሪዎቻችንን የእኛን ሰራተኞች በመቅረጽ ረገድ ትርጉም ያለው ሚና እንዲወጡ እናደርጋለን።

d. በየሩብ ዓመቱ የስልጠና ማጠናቀቂያ ግምገማ በማድረግ፣ መደበኛ የክህሎት ኦዲት እና ለስፔሻሊስት ሚናዎች ተከታታይ እቅድ በማውጣት፣ ይህንን ከአገልግሎት እቅዶችን ጋር በቀጥታ በማያያዝ የሰራተኞችን እድገት ከፍተኛው የበላይ አመራር።

## 19 አስተዳደር እና የአፈፃፀም ክትትል

a. የ 2019 የአስተዳደርና የምርመራ ማዕከል ያቀረበውን ምክረ ሀሳብ በመቃኘት፣ የአስተዳደር አሰራራችን ላይ እንዲሳተፉ ከነዋሪዎች እና ከተመረጡ አባላት ጋር በመሆን መስራት እንቀጥላለን ።

b. ከነዋሪዎች ጋር የተሻለ ግንኙነት ለመገንባት የስርዓት ልምምድ ስልጠናዎችን በማስፋፋት፣ የፕሮግራሞች እና የአፈጻጸም አላማዎችን በመምራት የአመራር ባህላችንን እንቀይራለን።

c. ስለ አገልግሎቶቻችን እና ስለ ማህበረሰቦቻችን ትክክለኛ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለመተንተን እና ለመጠቀም የሚያስችል አጠቃላይ የመረጃ/ውሒብ ስትራቴጂ እናዘጋጃለን።

## 20 ነዋሪዎችን ማዳመጥ

a. የምክር ቤቱን የቅሬታ ማቅረቢያ ሂደት ሙሉ በሙሉ እና ከዳር እስከ ዳር እንገመግማለን፣ ይህም በነዋሪዎች ተሞክሮ፣ በአገልግሎት መስፈርቶች አፈጻጸም እና በማካካሻ እንዲሁም በእርምት እርምጃ ዓይነቶች ላይ ትኩረት እናደርጋለን። ገለልተኛ የሆነ ቅሬታ የማጣራት ሂደትን እና ቅሬታ ባቀረቡ ነዋሪዎች ላይ ቅጣት ሊጋጥም ይችላል የሚል ስጋትን በተመለከተ አማራጮችን በማፈላለግ ማካተት አለበት።

b. ከአማካሪዎች (በተለይ በማኅበራዊ ድህነት መስኮች ካሉ) ጋር የተጨማሪ ከፍተኛ መኮንኖችን ተሳትፎ እናረጋግጣለን፣ ይህም ቁልፍ የሆኑ አዝማሚያዎችን እና ችግሮችን ለመለየት የሚረዳ ይሆናል።

c. ከነዋሪዎች ጋር በመሆን የህዝብ ተሳትፎ ቻርተርን እና የዜጎችን ፓነል ሙሉ በሙሉ ለመገምገም ከነዋሪዎች ጋር በጋራ እንሠራለን፣ በውሳኔ አሰጣጥ ረገድ ኃይልን ስለመጋራት፣ ይበልጥ አሳታፊ ወደሆኑ አቀራረቦች ለመሸጋገር እና ቀጣይነት ያላቸው ክትትል እና ቊጥጥር ዘዴዎችን ግምት ውስጥ ለማስገባት እንሰራለን።

d. ተጨማሪ የጋራ ዲዛይን እና ሌሎች የተሳትፎ አቀራረቦችን ለመተግበር እንሞክራለን (ለአብነት እንደ " የሕግ አውጭ ቲያትር" ያሉ አቀራረቦችን በቅርቡ በጊዜያዊ ማረፊያ ውስጥ ባሉ ነዋሪዎች ላይ ጥቅም ላይ ይውላል)።

# የምክር ቤቱ ባህል እና ከነዋሪዎች ጋር ያለው ግንኙነት

21 እነዚህን 10 ጭብጦች ባለፈው ወር ውስጥ ከነዋሪዎች ጋር ተወያይተንባቸዋል እንዲሁም በምርመራዉ የተለዩ የተወሰኑ የጉድለቶች ማስረጃዎችን፣ ተግባራዊ ያደረግናቸውን ለውጦች ማጠቃለያ እና በእያንዳንዱ አካባቢ መሻሻል ለማድረግ የሚያስችሉ አንዳንድ መነሻ ሐሳቦች አካፍለናል። አንዳንድ ነዋሪዎች ያደረግናቸውን ለውጦች አይተው እና አስተውለውም ነበር። ይሁን እንጂ ብዙዎች እንዳልታያቸዉ ነግረዉናል ወይም ለእነሱ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ነገር ለመፍታት እንዳልቻለ ነግረውናል።

22 ነዋሪዎች ቋሚ በሆነ መልኩ በመኖሪያ ቤትና በሌሎች አገልግሎቶች ላይ፣ በተመረጡ አባላትና ባለስልጣናት አመለካከትና ጠባይ ላይ፣ በዘርና በማህበራዊ አድልዎ ላይ ያላቸው ተሞክሮ መጥፎ መሆኑን እንዲሁም ለነዋሪዎቻቸውና ለተመረጡ ወኪሎቻቸው ሥልጣንን እና የውሳኔ አሰጣጥን ለመጋራት ፈቃደኛ አለመሆናቸው አሳስበዋል። አንዳንዶች ምክር ቤቱ ስለእነሱ በቂ ትኩረት እንደማይሰጥ እና አድልዎ እንደተደረገባቸው ሆኖ እንደሚሰማቸው ነግረውናል።

23 እነዚህ ተሞክሮዎች ምርመራዉ ላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ ችግሮች የሚያንጸባርቁ ናቸው ። ከግሬንፌል (Grenfell) አደጋ በፊት፣ የከተማዋ ነዋሪዎች አመለካከት ችላ ይባል ወይም ዝቅ ተደርጎም ይታይ ነበር፣ የዕለት ተዕለት ጉዳዮቻቸው ይናቁና ወደ ጎን ገሸሽ ይደረጉም ነበር፣ እንዲሁም ለእነሱ ምክንያት ተገቢ በሆነ ክብር እና አግባብ ባለው መንገድ አይያዝም ነበር። ምንም እንኳን ለውጥ ብናደርግም እነዚህ መሰረታዊ ችግሮች መቀጠላቸውን ነዋሪዎች የነገሩን ሲሆን በማህበራዊ መኖሪያ ቤት ውስጥ ያሉ ሰዎችን አያያዝ እንዲሁም ዘርን፣ የአካል ጉዳትንና ማህበራዊ አድልዎን በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎችን በጥልቅ እንድንገመግም ጠይቀዉናል።

24 የሕዝብ ውይይት መድረኮቹ በምክር ቤቱና በአንዳንድ የማህበረሰባችን ክፍሎች መካከል በተለይም በሰሜን ኬንሲንግተን (North Kensington)፣ ያለውን ልዩነት እንዲሁም በምክር ቤቱ ላይ ያለ እምነት ማጣት ጎላ አድርገው የሚገልጹ ናቸው ። በአደጋው ሐዘን የደረሰባቸው፣ከአደጋው በሕይወት የተረፉ፣ ነዋሪዎች እና የተመረጡ አባላት እነዚህን ጉዳዮች አንስተዋል፣ ነገር ግን የምርመራ ሪፖርት ከወጣበት ጊዜ አንስቶ የተደረጉ ውይይት ይበልጥ ትኩረት ሰጥቷቸዋል። ሰዎች በመተማመን ጉዳይ ላይ በጥልቅ እንድናስብ እንዲሁም ገለልተኛ የሆነ የመከራከርያ እና መቆጣጠርያ ፎርም እንድንጠቀም ጠይቀዉናል።

25 ስለዚህ በዚህ ምክር ቤት ውስጥ ስላለው ባህል ገለልተኛ የሆነ የውጭ ግምገማ **እንዲያካሂድ ሀሳብ እናቀርባለን**፣ በዋናነት ከነዋሪዎቻችን ጋር ያለውን ግንኙነት ከመመርመሩ በፊት (በተለይ በምክር ቤቱ የመኖሪያ ቤት እና ጊዜያዊ ማረፊያ እየኖሩ ያሉት እና የምክር ቤቱ ድጋፍ በሚያስፈልጋቸው ሌሎች ላይ ትኩረት በማድረግ)። የዚህግምገማ ወሰን ከተመረጡ አባላትና ነዋሪዎች ጋር ዉይይት ተደርጎበት ስምምነት ላይ ይደረስበታል፣ እንዲሁም እስከዛሬ በተሰጣቸው የማህበረሰብ አስተያየት ላይ በመመስረት፣ በዘርና በማህበራዊ አድልዎ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችን ያጤናል።

26 ነዋሪዎቹ ምክር ቤቱ ምን ዓይነት ባህል እንዲኖረው እንደምንፈልግ እንድንገልጽ ጠይቀውናል። በፍትሃዊነት፣ በአክብሮት እና ሰብዓዊነት ላይ የተመሰረተ ድርጅታዊ ባህል መገንባት እንፈልጋለን። በምክር ቤቱ ላይ አመኔታ ያለው ማንኛውም ሰው – የኋላ ታሪኩ ምንም ይሁን ምን - እንዲያዳምጡት፣ እንዲንከባከቡት እና እንዲረዱት እንፈልጋለን። ከነዋሪዎች ጋር በተለይም በማህበራዊ መኖሪያ ቤታችን ወይም በጊዜያዊ ማረፊያ ውስጥ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር እንፈልጋለን። ከግሬንፌል (Grenfell) ጋር በተያያዘ በምክር ቤቱ ልንፈጥረው የምንፈልገው ቅርስ ይህ ነው።

# ክትትል እና ተጠያቂነት

27 በሦስት ወራት ውስጥ ምላሽ መስጠት ትልቅ ጉጉት ያለው ተልዕኮ ቢሆንም ምክር ቤቱ ከግሬንፌል ትምህርት ለመማር በሙሉ ልብ ያለውን ቁርጠኝነት ለማሳየት ያለመ ነዉ። አንዳንድ ጊዜ ይህ ሁኔታ በምክር ቤቱና በማኅበረሰቦቹ ሙሉ በሙሉ ማማከርና መመርመር የሚያስፈልጋቸውን ሐሳቦች ሙሉ በሙሉ የማዘጋጀት ችሎታችንን ይገድበዋል። በ 2025 መጀመሪያ ላይ የጊዜ መለኪያዎችን፣ ኃላፊነቶችንና ተጠያቂነትን የሚያስቀምጥ ዝርዝር የድርጊት እቅድ እናወጣለን።

28 ምላሻችንም ለነዋሪዎች ቀጣይነት ያለው የግልጽነት እና የተጠያቂነት ከፍተኛ ደረጃ መኖርን ይጠይቃል። የለውጥ ግስጋሴን የመከታተል አሰራራችን ከላይ የተጠቀሱት ሦስት ዋና ዋና መርሆችን ታሳቢ ሊያደርግ ይገባል፡- የነዋሪዎች ኃይል እና ተሳትፎን፣ ገለልተኛ ምርመራ እና ቁጥጥር እንዲሁም ከፍተኛ ስታንዳርድ እና የቴክኒክ ችሎታ።

29 በሚኖሩን ለውጦች ውጤታማ የሆነ የነዋሪ ተሳትፎ፣ እና ቀጣይነት ያለው ክትትል ለማረጋገጥ፡-

a. ገለልተኛ **የምክክርፓናል**፣ በማህበራዊ መኖሪያ ቤት፣ ደህንነት፣ የደንበኞች አገልግሎት፣ የእድሳት ተግባራት እና ድርጅታዊ ለውጥ ባሉ መስኮች ተሞክሮ ያላቸው በአደጋው ሀዘን የደረሰባቸው፣ ከአደጋው በሕይወት የተረፉ፣ ነዋሪዎች እና ስፔሻሊስት ባካተተ መልኩ እንዲዘጋጅ ምክረ ሀሳብ እንሰጣለን። ይህ ቡድን በዚህ ሪፖርት ላይ የተቀመጠውን ድርጊት በራሱ እንዲቆጣጠር እና ምክር ቤቱ ለውጪያዊ ፈተና፣ ምክርና ክትትል ክፍት ሆኖ እንዲቀጥል በማድረግ ለዋናው አስተዳደርና የአስተዳደር ቡድን ምክር ይሰጣል። የቡድኑ የማመሳከሪያ ሐሳብ ከነዋሪዎቹና ከተመረጡ አባላት ጋር ይብራራል ስምምነት ላይም ይደረስበታል፤ ይሁን እንጂ ቡድኑ የባህል ገለልተኛ ግምገማ ያቀረብነውን ሐሳብ በበላይነት እንዲመራ ምኞታችን ነው። ከቡድን አባላት ጎን ለጎን የእኛን የእድገት ግስጋሴ ለመገምገም ከሚፈልግ ማንኛውም ነዋሪ ጋር አዘውትረን ለመተባበር የሚያስችል ፕሮግራም ይኖረናል።

b. የተጠናከረ **የቁጥጥርዝግጅት** በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጡ አባላቱ የምክር ቤቱ ውሳኔ አወሳሰድ እና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ውጤታማ ቁጥጥር እና ምርመራ በማድረግ ረገድ ቁልፍ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ። ይህም ባሕልን በራሳቸው መመርመርንና ከላይ ከተገለጸው ነፃ አማካሪ ቡድን የተገኙ ቋሚ የለውጥ ግስጋሴ ሪፖርቶችን መመርመርን ይጨምራል ። ለኮሚቴው የሚቀርቡ ሪፖርቶች የተደረጉትን ለውጦች በተመለከተ ጠንካራና ጥራት ባላቸው መረጃዎች የሚመሠረት ከመሆኑም በላይ በድርጊቱ እቅድ ላይ ስለተደረገው እድገት በየሦስት ወሩ የሚወጡ ማሻሻያዎችን ይጨምራሉ።

c. **ከውጫዊ ክትትል አድራጊ ጋር ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፡-** በሕግ የተደነገጉ ደንቦችን እና ምርመራዎችን እንዲሁም በአካባቢው የመንግሥት አካል የሚሰጥ ድጋፍ እና ማረጋገጫን በማካተት። በግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ላይ የደረሰው አሳዛኝ ክስተት ባስከተለው ጉዳት ምክንያት በአዲስ መልክ የተደነገገው መሥፈርትን ለማሟላት ከሕንፃ ደህንነት አስተዳዳሪና ከማኅበራዊ መኖሪያ ቤት አስተዳዳሪ ጋር ተቀራርበን እንሠራለን። በለንደን የአይበገሬነት አቅም (London Resilience) አማካኝነት ለአስቸኳይ ጊዜ እቅድ ዝግጅታችን የውጪ ማረጋገጫ እንዲሰጠን እንፈልጋለን፣ እንዲሁም በአካባቢው መንግስት ህብረት የእኩዮች ክትትል ፕሮግራም መሳተፋችንን እንቀጥላለን።

**d.** ከህብረተሰቡ: ከሰራተኞች እና ከተመረጡ አባላት ጋር (ነፃ አማካሪ ቡድንን በማካተት) አንድ ፕሮግራም ለመቅረጽ መስራት **ከግሬንፌል መማር**:ሰራተኞች: ነዋሪዎች እና አማካሪዎች እርስ በእርስ የመማር አጋጣሚዎች: በከተማ አዳራሽ ውስጥ ሊከናወነው የሚችል መታሰቢያ እና መማር ለሌሎች ድርጅቶች ጋር ትምህርት የመካፈል መንገዶች።

## መደምደሚያ

30 የግሬንፌል ታወር ምርመራ ሪፖርት 18 ሕፃናትን ጨምሮ 72 ሰዎች ለሕልፈተ ሞት ምክንያት የሆኑ ስህተቶችን ዘርዝሮ ነበር ። ይህ ሪፖርት የእነሱን ማስታወሻ ለማክበር ያለን ምኞት መግለጫ ነው። ነዋሪዎች ተጨማሪ ለውጥ ለማየት እንደሚጓጉ እንረዳለን፤ ነገር ግን እዚህ ላይ የቀረቡ ተሃድሶዎችና ቃልኪዳኖች መሠረታዊና ለመተግበር ጊዜ የሚወስዱ መሆናቸውን መገንዘብ አለብን። መደበኛ ውሳኔ የመስጫ መንገድ የተከተለ እና በነዋሪዎች የተቀረጹ እና በጥብቅ ተፅዕኖ ግምገማዎች ያለፉ የተወሰኑ ለውጦችን ለመንደፍ እና ለማሳካት ተጨማሪ ሥራ ያስፈልጋል። አተገባበሩንም ለአመራር ቡድን፣ ለአጠቃላይ እና ለምርመራ ኮሚቴ፣ እና ለሙሉ ምክር ቤት፣ እንዲሁም ለውጫዊ ምርመራና ክትትል በቀረቡ አሠራሮች አማካኝነት መደበኛ የሕዝብ ሪፖርት በማቅረብ በበላይነት ክትትል ይደረግበታል።

31 ይህ ሪፖርት ምክር ቤቱ ለምርመራዉ ሪፖርት የሰጠው ምላሽ ነው። የምላሻችን የኋላ ዳራ፣ የተከተልነው አቀራረብ፣ በአደጋው ሀዘን ካጋጠማቸው፣ ከአደጋው በሕይወት ከተረፉ፣ ከነዋሪዎች እና ከተመረጡ አባላት የተሰጡ አስተያየቶች ቁርጠኝነታችንን ቀርፀዋል። ከላይ ለተጠቀሰው ለእያንዳንዱ 10 ዋና ዋና መስኮች፣ በምርመራ ሪፖርት ላይ የተጠቀሱትን ዋና ዋና ስህተቶች፣ ከ2017 ወዲህ ያደረግናቸውን ቁልፍ ለውጦችና ተጨማሪ ማሻሻያ ማድረግ የሚያስፈልግባቸውን አቅጣጫዎች ይዘረዝራል። በመጨረሻም መንግሥት ለጥያቄው የሰጠዉ የመጨረሻ ምላሽ አንፃር በቀጣይ ክትትልና ተጠያቂነት ላይ የሚደረገውን አቀራረብና እዚህ ላይ የተቀመጠውን ቃል ኪዳን ለመከለስ እቅድ ይዟል።

32 ይህ ሪፖርት የመጨረሻ ነጥብ ባይሆንም ምክር ቤቱ ማስተካከያ ለማድረግና ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ሊወስደው የሚገባ ሌላ እርምጃ ነው ። የዚህ ምላሽ ስኬታማነት ውሎ አድሮ ነዋሪዎቹ ምክር ቤቱ ጋር ባላቸው ግንኙነት እውነተኛ ለውጥ ማየት ሲችሉ እና ሲሰማቸዉ የሚለካ ነዉ። ማህበረሰባችን ያንን ለውጥ እዉን ለማድረግ እና ይህን ለውጥ ለማድረስ ተጠያቂ እንድንሆን ከእኛ ጋር እንዲሠሩ እንጋብዛለን።

©2024 የኬንሲንግተን እና ቼልሲ ምክር ቤት (ዲሴምበር) የስራዉ ማጣቀሻ:- 1782_COP